ይህ መገልገያ (መፅሐፍ) የተጫነው
በ ኢትዮ_ Students የ ቴሌግራም ቻናል ላይ ነው



ከ10,000 በላይ ተማሪዎች ወቅታዊ መፅሀፍት እና ተማሪዎችን የሚረዱ ጥቅም አላቸው ፅሁፎችን ያገኛሉ

በቴሌግራም በርካታ ተከታዮች ያሉት ይፋዊ ቻናል

Join Us On @ethiostudente

አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ
የስምንተኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ሞዴል ፈተና
2012/2020

የጥያቄ ብዛት:- 60 **የተፈቀደው ጊዜ:-** 1 ሰዓት

መመሪያ አንድ:- **ከተራ ቁጥር 1 እስከ 10 ድረስ ቃላትንና ሐረጋትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጥያቄዎች የቀረቡበትን መንገድ መሰረት በማድረግ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከአማራጮ መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።**

1. «ወ/ሮ አቻምየለሽ ዛሬ <u>ሽምግልና</u> አለባቸው» በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ዐውዳዊ ፍቺው ምንድን ነው?

   A. እርጅና
   B. ዳኝነት
   C. ድካም
   D. ምርቃት

2. አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በየዓመቱ በርካታ ተማሪዎችን <u>ያስመርቃል</u>። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ዐውዳዊ ፍቺው ምንድን ነው?

   A. ስንብት ያደርጋል
   B. መመሪያ ይሰጣል
   C. ምስጋና ያቀርባል
   D. ብቁ ያደርጋል

3. «ጠብታ» በሚለው ቃል ውስጥ የሚገኘው "ብ" ፊደል ላልቶ መነበብ ያለበት በየትኛው ዓረፍተነገር ውስጥ ነው?

   A. ጥጃዋ ወተቷን ጠብታ ሜዳው ላይ ትቦርቃለች።
   B. ልብሴ ላይ ያረፈው የቀለም ጠብታ መንችኮ ቀረ።
   C. አላስፈላጊ የውሃ ጠብታ መቆም አለበት።
   D. ለትውልድ የስልጣኔ ጠብታ ማስቀመጥ መልካም ነው።

4. «አያት» በሚለው ቃል ውስጥ ያለው «ያ» ፊደል ላልቶ መነበብ ያለበት በየትኛው ዓረፍተነገር ውስጥ ነው?

   A. ከቤተሰቦቿ ጋር ሰብሰብ ብላ አያት።
   B. አያት ስለሌላት ደስተኛ ናት።
   C. ስትተውን አያት።
   D. አያት ግን አላናገራትም።

5. ከሚከተሉት መካከል «ድንጋይ» የሚለው ቃል በተለየ ዐውድ የገባው በየትኛው ዓረፍተነገር ውስጥ ነው?

   A. የተስተካከለ ድንጋይ የቤት ግድግዳ ይሆናል።
   B. ድንጋይ ላይ ተቀምጦ የጠዋት ፀሐይ ሲሞቅ ነበር።
   C. ድንጋይ አዕምሮውን ለመሞረድ ጊዜ ወስዷል።
   D. ድንጋይ በመጥረብ ይተዳደሩ ነበር።

6. ከመሬቱ ላይ የመኻታ ከረጢቱን አንጥፌ ጋደም <u>አስባልኩ</u>። ይህንን ዓረፍተነገር ለማስተካከል የተሰመረበት ቃል ቅርፁ እንዴት መጻፍ አለበት?

   A. ተባባልኩ
   B. አባባልኩ
   C. ተባልኩ
   D. አልኩ

7. ከሚከተሉት መካከል «ብትጠቀመው» የሚለው ቃል በትክክል ተነጣጥሎ የተፃፈው በየትኛው አማራጭ ነው?

   A. ብት-ጠቀመ-ው
   B. ብ-ት-ጠቀመ-ው
   C. ብት-ጠቀመው
   D. ብ-ት-ጠቀመው

8. ከሚከተሉት መካከል «በተደረደሩበት» የሚለው ቃል በትክክል ተነጣጥሎ የተፃፈው በየትኛው አማራጭ ነው?

   A. በተደረደሩ-በ-ት
   B. በ-ተ-ደረደሩበት
   C. በ-ተ-ደረደር-ኡ-በት
   D. ብ-ት-ጠቀመው

9. «የያዘው <u>አባዜ</u> አልለቅ ብሎት ያከንፈዋል» በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ተመሳሳይ ፍቺው ምንድን ነው?

A. አመል
B. ዕድል
C. እጣ ፈንታ
D. እጣ ጦስ

10. <u>ጥሮና ግሮ</u> ስኬታማ ለመሆን ብሩህ ሀሳቦችን ማሰብ ይጠይቃል። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ለተሰመረበት ሐረግ ተቃራኒ ፍቺ የሚሆነው ከሚከተሉት መካከል የትኛው ነው?

A. በስራ
B. በጥረት
C. በአጋጣሚ
D. በምኞት

መመሪያ ሁለት:- ከተራ ቁጥር 11 እስከ 20 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ምንባብ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ምንባቡን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል የተሻለውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።

አንድ ጅብ በሩቅ አህያ ተመለከተና ሊበላው ወሰነ። እየሮጠም ወደአህያው ተጠጋ። ጅቡን የተመለከተው አህያም ማምለጥ እንደማይችል ተረዳ። ድንገት አንድ ብልሀት ወደአዕምሮው መጣለት። እያነከሰ ለመሸሽ ሞከረ። ጅቡ ደረሰበትና አህያውን **ከመዘርጠጡ** በፊት፣ "ምናባክ ሆነህ ነው የምታነክሰው?" ሲል ጠየቀው። አህያም "ጌታዬ! ገደል ስዘል እሾህ ወግቶኝ ነው። እግሬ ውስጥ የገባው እሾህ በጣም መርዘኛ ነው፤ ልትበላኝ ከፈለክ መጀመሪያ ከእግሬ ውስጥ የገባውን እሾህ ንቀልልኝ። ምክንያቱም እሾሁ በጣም መርዘኛ ከመሆኑ የተነሳ በምትበላኝ ጊዜ ይወጋህና ይጎዳሀል። የሚሻለው መጀመሪያ ነቅለህልኝ ብትበላኝ ነው፤" አለው።

ጅቡም በምክሩ ስለተስማማ ከአህያው ስር ቁጭ አለና እሾሁን ለማውጣት በአፉና በምላሱ መደባበስ ጀመረ። በዚህ ጊዜ አህያው ጅቡን በሀይለኛ እርግጫ **ሲያቀምሰው** ጥርሱ እርግፍግፍ አለ። አሁን አህያና ጅብ እኩል ሆኑ። በምኑ ይብላው? በዚህ ጊዜ አህያው በጣም ይደሰትና "ብልጥ ሲያመልጥ አየኸው?" በማለት ሳቀበት።

11. በምንባቡ ውስጥ ዕኩይ ባህሪ ተላብሶ የቀረበው ማን ነው?

A. እሾህ
B. አህያ
C. ጅብ
D. እግር

12. በምንባቡ ውስጥ አህያው የተላበሰው ባህሪ ምን ዓይነት ነው?

A. አታላይ
B. ሞኝ
C. ብልሕ
D. ስግብግብ

13. ከሚከተሉት ምሳሌያዊ አነጋገሮች መካከል ጅቡን በተሻለ ሁኔታ የሚገልጸው የትኛው ነው?

A. ጅብ እስኪነክስ ያነክስ
B. ሞኝ ቢሸከም የበላ ይመስለዋል
C. አያ ጅቦ ሳታመካኝ ብላኝ
D. ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ

14. ምንባቡ ከየትኛው የሥነጽሑፍ ዘውግ ይመደባል?

A. ከአጭር ልቦለድ
B. ከተረት
C. ከቀልድ
D. ከመነባንብ

15. በምንባቡ መሰረት አህያ ጅቡን «ጌታዬ!» ብሎ የጠራው ለምንድን ነው?

A. በእድሜ ስለሚበልጠው
B. ጅብ የተከበረ እንስሳ ነው ብሎ በማሰቡ
C. አዝኖለት እንዲተወው
D. ያከበረው እንዲመስለው

16. በምንባቡ ውስጥ «ሲያቀምሰው» የሚለው ቃል አገባባዊ ፍቺው ምንድን ነው?

A. ሲልሰው
B. ሲገፋው
C. ሲያጎርሰው
D. ሲመታው

17. በምንባቡ መሰረት ጅቡ በአህያው ምክር የተስማማው ለምንድን ነው?

A. አህያው ከእኔ የተሻለ አዋቂ ነው ብሎ በማመኑ
B. ጅቡ ጉልበት እንጅ ብስለት ስለሌለው
C. እሾሁ በአህያው እግር ላይ ይታይ ስለነበር
D. የአህያው ዘዴ ቢገባውም ምንም እንደማይመጣ ስላወቀ

18. ከሚከተሉት መካከል የምንባቡን መልዕክት በተሻለ የሚገልፀው የትኛው ሀሳብ ነው?

A. ነገሮችን በብልሃት መምራት እንደሚያስፈልግ
B. ጅብ ምንም ዓይነት ብስለት የሌለው መሆኑን
C. አህያ ጠንካራ ከመሆኑ ባሻገር በሳልም መሆኑን
D. ጠላትን ከኋላ ከማድረግ መጠንቀቅ እንደሚያስፈልግ

19. በምንባቡ መሰረት «ከመዘርጠጡ» የሚለው ቃል አገባባዊ ፍቺው ምንድን ነው?

A. ከማሸተቱ
B. ከመርገጡ
C. ከመብላቱ
D. ከመጣሉ

20. ከሚከተሉት መካከል በምንባቡ ውስጥ የምክንያትና የውጤት ትስስር ያለው ዓረፍተነገር የትኛው ሀሳብ ነው?

A. ጅብ እየሮጠ ወደአህያው ተጠጋ።
B. ጅብ አህያውን ተመለከተና ሊበላው ወሰነ።
C. አህያውን የወጋው እሾህ መርዛማ ነበር።
D. አህያው ጅቡን በሀይለኛ እርግጫ አቀመሰው።

መመሪያ ሦስት:- ከተራ ቁጥር 21 እስከ 32 ድረስ የተለያየ ይዘት ያላቸው ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።

21. ከሚከተሉት መካከል የውይይት አቀራረብ መመሪያ **ያልሆነው** የትኛው ነው?

A. የውይይቱን ርዕስ መገንዘብ
B. የውይይቱን ዓላማ ለአድማጭ ማስተዋወቅ
C. በቂ ምክንያት ማቅረብ
D. ሀሳባችን በሌሎች እንዲገለፅልን መፍቀድ

22. ከሚከተሉት መካከል ቃለ መጠይቅ በሚካሄድበት ወቅት መከናወን ያለበት የትኛው ተግባር ነው?

A. ከቃለ መጠይቁ የሚገኘውን ምላሽ በማስታወሻ መመዝገብ
B. ለቃለ መጠይቁ አስፈላጊ የሆኑ አካላትን መለየት
C. ለቃለ መጠይቁ ትብብር ያደረጉ አካላትን ማመስገን
D. ለቃለ መጠይቁ የሚሆኑ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት

23. ከሚከተሉት መካከል ክርክር ከመካሄዱ በፊት መተግበር ያለበት የትኛው ተግባር ነው?

A. የመከራከሪያ ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም
B. የመከራከሪያ ሀሳቦችን ማደራጀት
C. ተራን ጠብቆ መከራከር
D. የዳኞችን ውሳኔ መቀበል

24. ስለሴቶች እኩልነት ከማውራታችን በፊት ለሴቶች ጫና በሆኑ ጉዳዮች ላይ እንወያይ። ለዚህ ውይይት እንዲያግዘንም ዓርአያ የሚሆኑ ሴቶችን ጋብዘን እዚህ ይገኛሉ።

በዚህ ሀሳብ መሰረት ድርጊቶች በቅደም ተከተል ሲቀመጡ የትኛውን ይሆናሉ?

A. ዓርአያ የሚሆኑ ሴቶችን መጋበዝ፣ ዓርአያ የሚሆኑ ሴቶች እዚህ መገኘት፣ ለሴቶች ጫና በሆኑ ጉዳዮች ላይ መወያየት፣ ስለሴቶች እኩልነት መወያየት
B. ዓርአያ የሚሆኑ ሴቶች እዚህ መገኘት፣ ዓርአያ የሚሆኑ ሴቶችን መጋበዝ፣ ለሴቶች ጫና በሆኑ ጉዳዮች ላይ መወያየት፣ ስለሴቶች እኩልነት መወያየት
C. ለሴቶች ጫና በሆኑ ጉዳዮች ላይ መወያየት፣ ስለሴቶች እኩልነት መወያየት፣ ዓርአያ የሚሆኑ ሴቶችን መጋበዝ፣ ዓርአያ የሚሆኑ ሴቶች እዚህ መገኘት
D. ስለሴቶች እኩልነት መወያየት፣ ዓርአያ የሚሆኑ ሴቶችን መጋበዝ፣ ዓርአያ የሚሆኑ ሴቶች እዚህ መገኘት፣ ለሴቶች ጫና በሆኑ ጉዳዮች ላይ መወያየት፣

ትዕዛዝ አንድ:- ተራ ቁጥር 25ን እና 26ን ቀጥሎ በቀረበው ምልልስ መሰረት መልስ/ሽ!

«የወደድኩሽ ይመስለኛል» አላት ማርቆስ እንደቀላል ነገር ማፍቀሩን እየወረወረላት፡፡
«ምን?» አለች ሰብለ መልስ ጠብቃ ሳይሆን የሰማችውን ባለማመን፡፡ መቀራረባቸው ወዴት እንደሚያመራ ለማወቅ እየጓጓች ስለነበር፡፡
«የወደድኩሽ ይመስለኛል» አላት አሁንም በድጋሜ፤ ቃላቶቹን ቀስ ብሎ እየደገመ፡፡ ሰብለ መልስ አልነበራትም፡፡ ዝም አለች፡፡ በዝምታ ውስጥ ደስ የሚል ስሜት ተሰማት፡፡

25. በዚህ ምልልስ መሠረት የሰብለ ስሜት ምን ይመስላል?

A. የማርቆስ ድፍረቱ ያናደዳት
B. ያልጠበቀችው ነገር የተፈጠረባት
C. መቀራረባቸውን የወደደችው
D. የማርቆስን ወንድምነት ያልተቀበለችው

26. በዚህ ምልልስ መሠረት ስለማርቆስና ስለሰብለ የትውውቅ ጊዜ ምን ማለት ይቻላል?

A. ረዘም ያለ ጊዜ ትውውቅ ያላቸው
B. አብረው ያደጉ
C. በድንገት ተያይተው የተራራቁ
D. በሀዘን ጊዜ የተያዩ

ትዕዛዝ ሁለት:- ከተራ ቁጥር 27 እስከ 29 ድረስ ያሉትን ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው የሰንጠረዥ መረጃ መሰረት መልስ/ሽ!

በ2006 ዓ.ም. ሊሰሩ የታሰቡ የአስፓልት መንገዶች			
ተ.ቁ.	የሚሰሩ መንገዶች	የተመደበ በጀት	ሥራው የሚጀመርበት ወር
1.	ከደብረብርሃን እስከ አንኮበር	88,500,000	ጥቅምት
2.	ከድሬደዋ እስከ ደወሌ	1,000,000,000	ጥር
3.	ከመሉጡሪ እስከ አለም ከተማ	100,000	ህዳር
4.	ከአሞ እስከ ማጅ	100,000	መጋቢት

27. በሰንጠረዡ መረጃ መሰረት ከሁሉም የአስፓልት መንገዶች መካከል ከፍተኛ በጀት የሚጠይቀው የትኛው ነው?

A. ከደብረብርሃን እስከ አንኮበር ያለው
B. ከድሬደዋ እስከ ደወሌ ያለው
C. ከሙከጡሪ እስከ አለም ከተማ ያለው
D. ከአሞ እስከ ማጅ ያለው


28. በሰንጠረዡ መረጃ መሰረት ከሁሉም የአስፓልት መንገዶች መካከል ቀድሞ የሚጀመረው የትኛው ነው?

A. ከደብረብርሃን እስከ አንኮበር ያለው
B. ከድሬደዋ እስከ ደወሌ ያለው
C. ከሙከጡሪ እስከ አለም ከተማ ያለው
D. ከአሞ እስከ ማጅ ያለው

29. በሰንጠረዡ መረጃ መሰረት ከሁሉም የአስፓልት መንገዶች መካከል ዘግይቶ የሚጀመረው የትኛው ነው

A. ከደብረብርሃን እስከ አንኮበር ያለው
B. ከድሬደዋ እስከ ደወሌ ያለው
C. ከሙከጡሪ እስከ አለም ከተማ ያለው
D. ከአሞ እስከ ማጅ ያለው

ትዕዛዝ ሦስት:- ከተራ ቁጥር 30 እስከ 32 ያሉትን ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው የግራፍ መረጃ መሰረት መልስ/ሽ!



30. በግራፉ መረጃ መሰረት የካንጋሮ ጫማ ፋብሪካ ከፍተኛ ምርት ያመረተው በየትኛው ወቅት ነው?

A. በአንደኛው ሩብ ዓመት
B. በሁለተኛው ሩብ ዓመት
C. በሦስተኛው ሩብ ዓመት
D. በአራተኛው ሩብ ዓመት

31. በግራፉ መረጃ መሰረት የካንጋሮ ጫማ ፋብሪካ የማምረቻ ጊዜውን መቀነስ ቢኖረበት የትኛውን ወቅት መተው ይመረጣል?

A. አራተኛና ሦስተኛ ሩብ ዓመታትን
B. ሦስተኛና ሁለተኛ ሩብ ዓመታትን
C. ሁለተኛና አንደኛ ሩብ ዓመታትን
D. አንደኛና አራተኛ ሩብ ዓመታትን

32. በግራፉ መረጃ መሰረት የካንጋሮ ጫማ ፋብሪካ ዝቅተኛ ምርት ያመረተው በየትኛው ወቅት ነው?

A. በአንደኛ ሩብ ዓመት
B. በሁለተኛው ሩብ ዓመት
C. በሦስተኛው ሩብ ዓመት
D. በአራተኛው ሩብ ዓመት

መመሪያ አራት:- ከተራ ቁጥር 33 እስከ 43 ድረስ ጽሕፈትን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።

33. «አቅጣጫ በግቢያችን የመኪና መብራት ይበራል።» ይህ ዓረፍተነገር ሀሳቡ ግልፅ እንዲሆን አወቃቀሩ እንዴት መሻሻል አለበት?

A. መብራት በግቢያችን አቅጣጫ የመኪና ይበራል።
B. በግቢያችን አቅጣጫ የመኪና መብራት ይበራል።
C. የመኪና መብራት ይበራል በግቢያችን አቅጣጫ።
D. በግቢያችን አቅጣጫ መብራት የመኪና ይበራል።

34. «የዕድገታቸው መነሻ የብዙ ሀገሮች ነባር ዕውቀት ነው» የሚለው ዓረፍተነገር አወቃቀሩ እንዴት መስተካከለ ይኖርበታል?

A. ዕውቀት የብዙ ሀገሮች የዕድገታቸው መነሻ ነባር ነው።
B. የዕድገታቸው መነሻ ነባር ዕውቀት የብዙ ሀገሮች ነው።
C. ሀገሮች የብዙ የዕድገታቸው መነሻ ነባር ዕውቀት ነው።
D. የብዙ ሀገሮች የዕድገታቸው መነሻ ነባር ዕውቀት ነው።

35. የተሸለ ሰው ሆና የተገኘችው ወገቧን አስራ በመማሯ ነው።
ከሚከተሉት መካከል ለዓረፍተነገሩ ውጤት መሆን የሚችለው የትኛው ነው?

A. ወገቧን ማሰር
B. ወገቧን አስራ መማር
C. የተሻለ ሰው ሆና መገኘት
D. መማር

36. «ብዕሩን እንደጦር መሳሪያ ሲጠቀመው ማሰብ እንደተሳነው አልተጠራጠረችም» በሚለው ሀሳብ ውስጥ በምክንያትነት የሚጠቀሰው የትኛው ነው?

A. ብዕሩን እንደጦር መሳሪያ መጠቀም
B. ማሰብ መሳኑ
C. አለመጠራጠሯ
D. ጦር አለመፍራቱ

37. «ሀገር ልትዳብር የምትችለው የሀገር ዕንቁ ሀብት የሆነው ህዝብ ሲዳብር ሲችል ነው» የዚህ ዓረፍተነገር ውጤት መሆን የሚችለው የትኛው ሀሳብ ነው?

A. ሀገር መዳበር
B. ህዝብ መዳበር
C. የሀገር ሀብት መኖር
D. የሀገር ዕንቁ መሆን

38. «የስልክ <u>ምልልሱ</u> ሰምቸዋለሁ» በሚለው አነጋገር ውስጥ የተሰመረበት ቃል ከሀሳቡ ጋር እንዲዋሀድ ቅርፀ እንዴት መስተካከል ይኖርበታል?

A. መልሱን
B. ምላሹ
C. ምልልሱን
D. መላሹ

39. ከሚከተሉት መካከል የህይወት ታሪክ ለመፃፍ አስገዳጅ **ያልሆነው** ተግባር የትኛው ነው?

A. ግለሰቡን በቅርበት ከሚያውቁት ሰዎች መረጃ መሰብሰብ
B. ስለግለሰቡ ከተፃፉ ጽሁፍ መረጃ መሰብሰብ
C. ግለሰቡ በህይወት ካለ ከራሱ መረጃ መሰብሰብ
D. መረጃዎችን በቅደም ተከተል ማደራጀት

40. ከሚከተሉት መካከል የህይወት ታሪክ ሲፃፍ መጨረሻ መፃፍ ያለበት የትኛው መረጃ ነው?

A. በ41 አመታቸው የካናዳ አምባሳደር ሆነው ተሹመዋል።
B. የሁለት ሴቶችና የአንድ ወንድ ልጅ እናት ነበሩ።
C. ከአባታቸው ከአቶ ውብሸት ማንደፍሮና ከእናታቸው ከወ/ሮ የውብዳር ሳህለ በ 1948 ዓ.ም. ተወለዱ።
D. በተወለዱ በ 79 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ።

41. ሀ. ሰነፍ ተማሪ አለ።
ለ. ተማሪ ዓይነት ዓይነት አለው።
ሐ. ምስጉን ተማሪ ከሰነፍ የሚለየው በስራውና በታታሪነቱ ነው።
መ. ምስጉን ተማሪ አለ።

እነዚህን ዓረፍተነገሮች አንድ አንቀፅ ለማድረግ ቅደም ተከተላቸው እንዴት ቢስተካከል የተሻለ ይሆናል?

A. ለ፣ ሐ፣ ሀ፣ መ
B. ለ፣ መ፣ ሐ፣ ሀ
C. ሀ፣ መ፣ ለ፣ ሐ
D. ለ፣ መ፣ ሀ፣ ሐ

42. «አንገትህን ወደሀገርህ ሜዳ አቅና» ለሚለው ስንኝ በዜም በሀሳብም በተሻለ መልኩ የሚስማማው ስንኝ ከሚከተሉት መካከል የትኛው ነው?

A. የጦር ውርወራ የጥይት እሩምታ
B. ቁም ነገር ሰርተህ በእምነትህ ጽና
C. ስትወጣ ስትገባ አትምታ ዳንኪራ
D. መንገዝ መንከራተት መቼ ሰለቸህና

43. ሰዎች እባካችሁ መድሃኒት ፈልጉ፣
እናንተም ታማችሁ እናንተም እናንተም።

ይህ ግጥም ስሜት እንዲኖረው የሀረግና የስንኝ ቅደም ተከተሉ እንዴት መስተካከል አለበት?

A. መድሃኒት ፈልጉ ሰዎች እባካችሁ፣
እናንተም እናንተም እናንተም ታማችሁ።
B. መድሃኒት ፈልጉ ሰዎች እባካችሁ፣
እናንተም ታማችሁ እናንተም እናንተም።
C. ሰዎች መድሃኒት ፈልጉ እባካችሁ፣
እናንተም እናንተም እናንተም ታማችሁ።
D. ሰዎች እባካችሁ ፈልጉ መድሃኒት፣
እናንተም ታማችሁ እናንተም እናንተም።

መመሪያ አምስት:- ከተራ ቁጥር 44 እስከ 49 ድረስ ሥርዓተነጥብን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።

44. ___አንተ ግን እስከመቼ በሌላ ሰው ጭንቅላት ትመራለህ? ከምትጎተት ለምን ራስህን አትችልም?_____ ስትል አምርራ ተናገረችው። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ላለው ክፍት ቦታ ተስማሚ የሚሆነው ሥርዓተነጥብ የትኛው ነው?

A. // C. ‹ ›
B. … D. ‹‹ ››

45. ማጎበረሰቡን የናቀ___ ያዋረደና ለጎሊናው ቦታ የሌለው ዜጋ ስልጡን ሊሆን አይችልም። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ላለው ክፍት ቦታ የትኛው ሥርዓተነጥብ ይስማመዋል?

A. ፣ C. !
B. i D. ፤

46. ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች መካከል የሥርዓተነጥብ አገባቡ ትክክል የሆነው የትኛው ነው?

A. ‹‹የእኔና የእህቴ ነፍስ ወደጥበብ ትጓዛለች፤ ትላለች እህቴ መመሳሰላችን እየገረማት::››
B. ‹‹የእኔና የእህቴ ነፍስ ወደጥበብ ትጓዛለች::›› ትላለች እህቴ መመሳሰላችን እየገረማት::
C. ‹‹የእኔና የእህቴ ነፍስ ወደጥበብ ትጓዛለች›› ትላለች እህቴ መመሳሰላችን እየገረማት::
D. የእኔና የእህቴ ነፍስ ‹‹ወደጥበብ ትጓዛለች›› ትላለች እህቴ መመሳሰላችን እየገረማት::

ትዕዛዝ አራት:- ከተራ ቁጥር 47 እስከ 49 ድረስ ያሉትን ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበዉ አንቀፅ መሰረት መልስ/ሽ!

«ምን ልታዘዝ 1 » አለ አስተናጋጁ ወደተስተናጋጁ ጎንበስ ብሎ::
«አንድ ቀዝቃዛ ቢራ» አለ ተስተናጋጅ:: «አትቀልድ እባክህ 2 ራሴን አሞኛል ስትል አልነበረም?» አለችው ወንድሟን አብራው ያለችው እህቱ:: በዚህ መልኩ ንግግር ከጀመሩ እንደማያቆሙ የገባው ወንድማቸው «እኔ መሄዴ ነው 3 ስትጨርሱ ደውሉልኝ» ብሏቸው ውልቅ አለ:: አስተናጋጁም ከአጠገባቸው ዘወር...

47. በተራ ቁጥር 1 ቦታ መተካት ያለበት ሥርዓተነጥብ የትኛው ነው?

A. ?
B. !
C. ፤
D. i

48. በተራ ቁጥር 2 ቦታ መተካት ያለበት ሥርዓተነጥብ የትኛው ነው?

A. ፣
B. ::
C. ፤
D. !

49. በተራ ቁጥር 3 ቦታ መተካት ያለበት ሥርዓተነጥብ የትኛው ነው?

A. ፤
B. ‹ ›
C. i
D. ፣

መመሪያ ስድስት:- ከተራ ቁጥር 50 እስከ 55 ድረስ ሰዋስውን የሚመለከቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበዋል። ለእያንዳንዱ ጥያቄ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።

50. ከሚከተሉት ዓረፍተነገሮች መካከል ዓይነቱ አሉታዊ የሆነው የትኛው ነው?

A. ውዳሴ ፈላጊው ብዙ ነው
B. ውዳሴ ፈላጊ መሆን አይገባም
C. ውዳሴ ፈላጊ ነህ ልበል
D. ውዳሴ ፈላጊ መሆን ለምን አስፈለገህ?

51. «እጆቿ የጥጥ አመልማሎ ይመስላሉ» በሚለው ዓረፍተነገር ውስጥ በመሙያነት የገባው ስማዊ ሐረግ የትኛው ነው?

A. የጥጥ
B. አመልማሎ ይመስላሉ
C. አመልማሎ
D. የጥጥ አመልማሎ

52. "ባለጉዳዩ" በሚለው ቃል ውስጥ እምር አመልካች ቅጥያው የትኛው ነው?

A. ባለ-
B. -ዩ
C. -ኡ
D. ለ-

53. እነዚህ ምስሎች የማንነታችን አሻራዎች ናቸው። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ጠቋሚ መስተኣምሩ የትኛው ነው?

A. የማንነታችን
B. አሻራዎች
C. ምስሎች
D. እነዚህ

54. ከሚከተሉት ቃላት መካከል የቃል ክፍሉ ቅፅል የሆነው የትኛው ነው?

A. ስብዕና
B. ችሮታ
C. ለስላሳ
D. እርጋታ

55. ወርቅነህ ዛሬ እዚህ ሰብሰባ ላይ ይሳተፋሉ። በዚህ ዓረፍተነገር ውስጥ ጊዜ አመልካች ተውሳከ ግስ የሆነው የትኛው ነው?

A. ወርቅነህ
B. ዛሬ
C. እዚህ
D. ሰብሰባ

መመሪያ ሰባት፡- ከተራ ቁጥር 56 እስከ 60 ድረስ ያሉት ጥያቄዎች ቀጥሎ በቀረበው ግጥም ላይ የተመሠረቱ ናቸው። ግጥሙን በጥሞና በማንበብ ለጥያቄዎቹ ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክል የሆነውን መልስ ምረጥ/ምረጪ።

ካልጋዬ ላይ ሆኜ በእንቅልፍ ስንጠራራ፣
ሰፈዴ ሃኬት ይገፍ ወሬዬን ስዘራ፣
ግብሬን ረስቼ ተግባሬን ሳልሰራ፣
ያው ጥሎኝ በረረ እንደንስር አሞራ።
ሰነፍ አይደርስበት እሯጭ አይቀድመው፣
ዘላለሙን ቢሄድ መስገር አይደክመው።
በስራ በትጋት ጠፍረው ካልያዙት፣
ጊዜ ፈረሰኛ ነው ምን ቢጠባበቁት።

56. የቀረበው ግጥም በስንት ስንኞች የተዋቀረ ነው?

A. 16
B. 8
C. 3
D. 1

57. በግጥሙ ውስጥ ጊዜ የተመሰለው በምንድን ነው?

A. በሀኬት
B. በመስገር
C. በፈረሰኛ
D. በንስር አሞራ

58. የግጥሙ ሦስተኛው ስንኝ ቤት የትኛው ነው?

A. ሳልሰራ
B. ራ
C. ረስቼ
D. ቼ

59. ከሚከተሉት መካከል በግጥሙ ውስጥ ቤት መድፊያ የሆነው ቃል የትኛው ነው?

A. ስንጠራራ
B. ስዘራ
C. ሳልሰራ
D. አሞራ

60. የግጥሙ መልዕክት ምንድን ነው?

A. ወሬ ተግባቦትን ያቀላጥፋል።
B. ከእንስሳቶች ሁሉ ለፍጥነቱ በቅሎ ይሻላል።
C. ጊዜያችንን በአግባቡ ካልተጠቀምን ስያልፍ ይቆጨናል።
D. ሰጋር በቅሎና ፈጣን ሯጭ የእግር አጣጣላቸው ይመሳሰላል።

የመጨረሻው ገፅ